ቁጥር፡- አ1162/11/15366

ጥር 2 ቀን 2017

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

**ለኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር**

**ሶማሌ**

የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ንቅናቄ(ኦብነግ) ከቦርዱ ሙሉ እውቅና አግኝቶ እየተንቀሳቀሰ ያለ ፓርቲ ሲሆን ጠቅላላ ጉባኤውን በ2015ዓ/ም ማድረግ ሲገባው እስከ አሁን ሳያደርግ ቆይቷል።

በአዋጅ 1162/2011 አንቀጽ 74/1/ሸ/ መሰረት አንድ ፓርቲ ቢያንስ በሶስት አመት አንዴ ጠቅላላ ጉባኤ ማካሄድ ያለበት በመሆኑ ደንግጓል። ይህንኑ ለማስፈጸም ቦርዱ በቁጥር፡ አ1162/11/14022 በጥቅምት 16/2016ዓ/ም እንዲሁም በመስከረም 28/2017ዓ/ም ለፓርቲው ቢያሳስብም እስካሁን ድረስ ፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ሳያደርግ ከ2 አመት በላይ አስቆጥሯል።

በሌላ በኩል የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር በ2016ዓ/ም መንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት እንዲችል የሴት እና የአካል ጉዳተኛ አባሎቻቸውን ቁጥር እንዲልክ ሲጠየቅ የተጋነነ መረጃ በመላኩ ቦርዱ የአባላቱን መታወቂያ በዲጂታል መንገድ እንዲልክ በቁጥር፡ አ1162/11/14743 መጋቢት 25/2016ዓ/ም ፤በቁጥር፡ አ1162/11/15136 በሐምሌ 15/2016ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ቢገለጽለትም ፓርቲው መረጃውን እስካሁን ሳይልክ ቀርቷል።

በዚሁ መሰረት ቦርዱ በጳጉሜ 5/20160ዓ/ም በ1 ወር ጊዜ ውስጥ መረጃዎቹን እንዲያቀርብ፤ ይህ ካልሆነ ታግዶ መከላከያውን እንዲያቀርብ የሚደረግ መሆኑን በቁጥር፡ አ1162/11/15252 በቀን 28/01/2017ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ቢያሳስብም ለቦርዱ ከፓርቲው የተላከ መረጃ የለም።

በመሆኑም ፓርቲው መረጃውን ያላቀረበ በመሆኑ ቦርዱ በታህሳስ 21/2017ዓ/ም የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 98/1/ሐ/ እና /ሠ/ መሰረት ታግዶ



አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚገን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

Scanned with CamScanner

የማይሰረዝበትን ምክንያት በ1 ወር ጊዜ ውስጥ እንዲያቀርብ በአንቀጽ 98/3/ መሰረት ቦርዱ ወስኗል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ተገቢውን መከላከያ ሳያቀርብ ቢቀር ቦርዱ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ሊሰጥ የሚገደድ መሆኑን በአክብሮት ቦርዱ ከወዲሁ ያሳውቃል።

**ከአክብሮት ሰላምታ ጋር!**

ውብሸት አየለ ጌጤ
Woubshet Ayele Gete
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ም/ሰብሳቢ
Deputy Chairperson National Electoral Board

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
የፖለቲካ ፓርቲዎች ዘርፍ

Scanned with CamScanner